## 1 ሻወር በምንወስድበት ወቅት



እጆቻችን ስለሚረጥቡና በቀላሉም በሰውነታችን ላይ ለመንሸራተት ስለሚችሉ በጣቶቻችን ጫፎች ሳይሆ ንበሙሉ ጣቶቻችን ጠንከር ባለ መልክ ጡቶቻችንን በመዳበስ መፈተሽ

- በግራ በኩል ያለውን ጡታችንን በቀኝ እጃችን እንዲሁም በቀኝ በኩል ያለውን ጡታችንን በግራእጃችን በመጠቀም መዳበስ ይኖርብናል

## ጡቶቻችንን በምንመረምርበት ወቅት የምንፈልገው ምንድን ነው?

ማንኛውንም የጠጠረና የእብጠት ምልክት መፈተሽ ይኖርብናል

## 2 መስተዋት ውስጥ በመመልከት የሚደረግ ምርመራ

- እጆቻችንን ወደታች በ ግራና በቀኝ ጎኖቻችን በኩል ዘርግተን በመቆ ም በጡቶቻችን ላይ በ ቅርቡ የተከሰቱ ለውጦ ችን መገንዘብ- የቅርፅና የመጠን ለውጥ፣ የእብ ጠትምልክት፤ በቆዳችን ላይየቀለም ለውጥ እን ዳለ መመልከት።እንዲ ሁም በጡቶቻች ጫፎ ች ላይለውጥ እንዳለም መመልከት።
- እጆቻችንን ወደላይ በመስቀል ከላይ የጠቀስናቸውን ለውጦች መፈለግ
- እጆቻችንን በዳሌያችን ላይአ ድርገን በመጎንበስ በመምጣትከ ጡቶቻችን ጫፍ የሚወጣ ፈሳ ሽ ነገር ካለ መመልከት። እንዲሁም በጫፎቹ ላይ ያለው ቆዳየተለየ መልክ እንዳለው መገንዘብ።







## 3 በጀርባችን በመጋደም ጡቶቻችንን ስለመመርመር



ጡቶቻችን ሙሉ በሙሉ በደረታችን ላይ እንዲዘረጉ በጀርባችን ከተንጋለልን በኋላ ለመመርመር ካሰብነው ጡታችን ባለው ትከሻችን ስር ትራስ ማድረግ

የቀኝ እጃችንን በመጠቀመም የግራ ጡታችንን፣ የግራ እጃችንን በመጠቀም የቀኝ ጡታችንን መርመር ይኖርብናል።

## የግራውና የቀኙ ጡታችን ተመሳሳይ መሆን አለበት ወይ?

- ጡቶቻችን የግራው ከቀኙ ጋ መመሳሰል የለባቸውም። መገንዘብና ማስተዋል ያለብን ከወር ወር በቅርፅና በመጠን ጡቶቻችን ተመሳሳይ መሆናቸውን ነው።

## ጡቶቻችንን በየወሩ መመርመር ለምን አስ ፈላጊ ሆነ?

- በየወሩ ጡቶቻችንን በግል በመመርመር የተፈጥሮ ቅርፃቸውንና እንዲሁም በተፈጥሮ ጠጣር የጡቶቻችንን ክፍሎችን ካወቅን ከእ ነዚህ የተለየ ነገር ሲያጋጥመን በቶሎ ወደ ሐ ኪም በመሄድ ተገቢውን እርዳታ እንድናገኝ ይረዳናል።

## የትኛውን የጣት ክፍል በመጠቀም ጡቶቻችንን መመርመር አለብን?



የቀለበት፤የመሃከልና የመጠንቆያ ጣቶቻችን በሆኑት በመሀከል በሚገኙ ት ሶስት ጣቶች በመጠቀ ም የጡቶቻችንን ምርመ ራ ማከሀሄድ አለብን።

## በምን አይነት መንገድ ጣቶቻችንን በማን ቀሳቀስ ጡቶቻችንን መመርመር አለብን?

- በመጀመሪያ ጠቅላላ ጡታችንን መመርመር አለብን። በተለይም በብብታችንና በትከሻችን አጥንት ስር ያለውን የጡታችንን ክፍል መፈተሽ እንዳንዘነጋ ያስፈልጋል።
- ከዚህ በታች ያለው ስእል ሶስት የተለያዩ የምርመራ ዘዴዎችን ያሳያል። ከሶስቱ ለእኛ የሚስማማንን ከመረጥን በኋላ የመረጥነውን ዘዴ በየወሩ በምናደርገው ምርመራ መጠቀም ይኖርብናል።



- ጡቶቻችንን ከላይ በተማለከቱት ዘዴዎች አንዱን በመምረጥ መመርመር አለብን።
- የጡቶቻችን ጫፎች በመመልከት ከጡቶቻችን የሚወጣ ፈሳሽ ነገር ንፁህ ወይንም በደም የተሞላ ፈሳሽ ካየን በቀጥታ ሐኪም ጋ በመሄድ መመርመር አለብን።
- አንዱን ጡታችንን ከመረመርን በኋላ በተመሳሳይ መንገድ ሌላኛውን ጡታችንን መመርመር እንዳንረሳ።
- በአንደኛው ጡታችን ላይ የተሰማንን ከሌላኛው ጡታችን ጋር ማመዛዘን ይኖርብናል።

Cross Cultural Health
crossculturalhealth.org